# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ዓርብ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም.

## የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን ቀጣይ ትግል መደገፍ ወሳኝ ነው

ዛሬ ዓርብ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም. በአዲስ አበባ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊም ወገኖቻ ችን ቢጫ ጨርቅ እያውለበለቡ (ቁጣዩ ቀይ መሆኑን በመጠቆም) ያደረጉት የተቃውሞ እንቅስቃሴ ን ሙሉ በሙሉ ኢሕአፓ እየደገፈ ሌሎችም የሕብረተሰቡ ክፍሎች ሁሉ በተግባር ድጋፋቸውን እን ዲያሳዩ ኢሕአፓ እንደገና ሀገራዊ ጥሪውን ያቀርባል ፤ያስተላልፋል ።

አለአግባብ በወያኔ ባለስልጣኖች ተይዘው በእስር ቤት እየማቀቁ የሃይማኖት መሪዎችና ዜጎች ባስቸ ኳይ እንዲፈቱ በመጠየቅና እንዲሁም በመስከረም 27 ቀን ወያኔ የራሱን ሰዎች ለማስቀመጥ ያቀደ ው ምርጫ ህገ ወጥ መሆኑን በማውገዝ ሕዝበ ሙስሊሙ ከፍተኛ የተቃውሙ እንቅስቃሴ አድርጓል። የወያኔ ሹመኞች የተካኑበትን የተንኮልና የጭካኔ ስራ በሙስሊም ወገኖቻችን ላይ ሲፈጽ ሙ ቆይተዋል። ካድሬዎቻቸውን በመላክ ሕዝበ ሙስሊሙ በምርጫው ካልተሳተፈና እነሱ የሚሉት ን ካልመረጠ የቀበሌ ቤት እንደሚነጠቅ፥ ተማሪው የትምህርት እድሉን እንደሚያጣ፥ የመንግስት ሰራተኞች ከስራ እንደሚባረሩ፥ ነጋዴው የንግድ ፈቃዱ እንደሚነጠቅ ሌሎችም የተለያዩ ችግሮች እንደሚደርስባቸው በመናገር ሲያስፈራሩ ሰንብተዋል። ይህን ሁሉ ሙስሊሙ ተቃውሟል፥ አውግዟ ል።

ሀገር አጥፊው አምባገነን ቢሞትም በምትኩ ስልጣን ይዘው ያሉት ጓደኞቹና ምናልባትም ከእሱ የባ ሱ ጠባብ ብሔረተኞችና ዘረኞች መሆናቸውን ሁሉም ዜጋው የሚያውቀው ነው ።ከፋፋዩና ዘረኛው ፖሊተካ ቀጥሏል ፤ በሀይማኖቶችና በአማኞች ላይ የሚደረገው ተፅዕኖና በደል አይሏል ። ሙስሊም ኢትዮጵያውያን በሀይማኖታችን ጣልቃ አትግቡ ፤ የታሰሩት ወገኖችም በአስቸኳይ ይፈቱ ብለው መነሳታቸውና ትግል መቀጠላቸው ተገቢና የሚደገፍምነው ። ሙስሊም ወገኖቻችን ለወያኔ ከፋፋይ ወጥመድ ሰለባ አልሆኑለትም ። ሌላውን የሚያስበረግግ ወይም የሚያስፈራራ መፈክሮችን ወይም ግ ቦችን አላስተጋቡም ። ዴሞክራሲን፤የሕዝብ መብትንና አንድነትን የሚፃረሩ መፈክሮች ቢወረወሩ ሕዝብም ድርጅቶችም የሚቃወሙና የሚታገሉ መሆናቸውንም ሁሉ ያውቃል ። የወያኔ አገዛዝ የ ሙስሊሞቹን ሰልፍ ያልሆነ ይዘት በመስጠትና ፅንፈኛ እያለ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ቀሪውን

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ሕዝብ ሊያስፈራራ ድጋፍም እንዳይሰጥ ለማድረግ እየተራወጠ ነው ። ለዚህ ሰለባ መሆን አሳዛኝ ክ ስተትከመሆኑ ባሻገር የሕዝብን ድል ጊዜ ያርቃል ። ቀሪው በከተማ ያለ የሕብረተሰብ ክፍል (ተማሪው አስተማሪው፤ ቢሮ ሰራተኛው ታክሲ ነጂው፤ ሳባደሩ፤ሴቱ ወንዱ ወዘተ) ሰልፈኞቹን ደግ ፎና የራሱንም ጥያቄዎች አንግቦ አርድ አንቅጥቅጥን አንቅስቃሴ ማሳየት አለበት ። ትግሉም ወደ ክ ፍለሀገርና ገጠሩ ሕዝብ መዳረስ መስፋፋት  አለበት ። ይህ ካልተደረገ ወሳኝየታሪክ ወቅት ያልፋል፤ ዘረኛውና አረመኔውም አገዛዝ ይቀጥላል ።

እጅ አጣጥፎ ተመልካችነት ምንም ማጠየቂያ የለወም--ጥፋት ስህተት እንለው እንደሆነ ነው እንጂ ። ተቃዋሚ ድርጅቶችም ከወየኔ ጋር እርቅ ይፈጠራል በሚል የምትሃት ተስፋ ከማሳደ ድ ይልቅ ሙስሊም ወገኖቻችንን በተጨባጭ መደገፍና ከጎናቸው መቆም ይገባቸዋል እንላለን ።

የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ በአስቸኳይ ይፈቱ !
ቀጣዩን የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን ትግል እንደግፍ !
በጋራ  በሕዝብን በሀገር ጠላቶች ላይ አንነሳ !!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France